ቀን፡ ሰኔ 20 ቀን 2018 ዓ.ም

ተ.ቁ፡ፓፔ/ቦዳ/ወጪ.ደ/0013/2026

**የጉባዔ ጥሪ ማስታወቂያ**

**የፓዋፔይ ዲጂታል ፋይናንሺያል አገልግሎቶች አክሲዮን ማህበር**

**የባለአክሲዮኖች 1ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ የጉባዔ ጥሪ**

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ንግድ ሕግ አዋጅ ቁጥር 1243/2013 አንቀጽ 366(1)፣ አንቀጽ 367፣ አንቀጽ 370፣ አንቀጽ 393 እና አንቀጽ 394 እንዲሁም በአክሲዮን ማህበሩ መመሥረቻ ጽሑፍ አንቀጽ 9.1 እና በዳይሬክተሮች ቦርድ ውሳኔ ቁጥር 01 መሠረት፣ የፓዋፔይ ዲጂታል ፋይናንሺያል አገልግሎቶች አክሲዮን ማህበር የባለአክሲዮኖች 1ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ (ዓመታዊ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ)፣ ሰኔ **24** ቀን **2018** ዓ.ም **(July 1, 2026)** ከ**4፡00** ሰዓት (ጥዋት) ጀምሮ በዳኒ ፕላዛ፣ 4ኛ ፎቅ፣ ወሎ ሰፈር፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 02፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ ይካሄዳል። በመሆኑም የተከበራችሁ የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች በሙሉ በጉባዔው ላይ እንድትገኙልን የማህበሩ የዳይሬክተሮች ቦርድ ጥሪውን በአክብሮት ያስተላልፋል።

ይህ ጉባዔ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በቁጥር ፋስ/ራሳአዳ/**359/26** በቀን ግንቦት **27** ቀን **2018** ዓ.ም በጻፈው የግብረ መልስ ደብዳቤ መሠረት፣ መጋቢት **18** ቀን **2018** ዓ.ም ተካሂዶ የነበረውን **1**ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ ሙሉ በሙሉ እንደገና ለማካሄድ የተጠራ መሆኑን እናሳውቃለን።

## 1. ማህበሩን የሚመለከቱ ዋና ዋና መረጃዎች

1.1 የአክሲዮን ማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት አድራሻ፦ ዳኒ ፕላዛ፣ 4ኛ ፎቅ፣ ወሎ ሰፈር፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 02፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፤ ስልክ፦ +251 912502619 ፤ ኢሜይል፦ support@pawapay.et፤ ድረ-ገጽ፦ pawapay.et

1.2 የአክሲዮን ማህበሩ የምዝገባ ቁጥር፦ የንግድ ምዝገባ ቁጥር MT/AA/3/0059249/2017፤ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ፈቃድ ቁጥር NPS-PSO/010/2024

1.3 የአክሲዮን ማህበሩ የተፈረመ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፦ 3,000,000.00 የኢትዮጵያ ብር (3,000 አክሲዮኖች፣ እያንዳንዳቸው 1,000 ብር)

1.4 የአክሲዮን ማህበሩ የተከፈለ ዋና ገንዘብ (ካፒታል)፦ 3,000,000.00 የኢትዮጵያ ብር (ሙሉ በሙሉ የተከፈለ)

## 2. የ1ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔ አጀንዳዎች

2.1 የጥሪ ማሳሰቢያ መተው ስምምነትን (Waiver of Notice) ማጽደቅ፤

2.2 የጉባዔ ሰብሳቢ፣ ድምጽ ቆጣሪዎች እና ጸሐፊ መሰየምን ማረጋገጥ፤

2.3 የመጀመሪያውን የዳይሬክተሮች ቦርድ ሹመት ማረጋገጥ፤

2.4 የዳይሬክተሮች ቦርድ ሪፖርትን መመርመርና ማጽደቅ፤

2.5 የፋይናንስ መግለጫዎችን ማጽደቅ፤

2.6 የውጭ ኦዲተር ሪፖርትን እና ለዋና ሥራ አስፈጻሚው የተደረገ የብድር ክፍያን ማድመጥ፤

2.7 የቁጥጥር ሁኔታ እና የዋና ሥራ አስፈጻሚ የሥራ አቅጣጫ፤

2.8 የዳይሬክተሮች እና የዋና ሥራ አስፈጻሚ ክፍያ፤

2.9 የውጭ ኦዲተር ሹመት እና ክፍያ፤

2.10 ሌሎች ጉዳዮች።

## 3. ማሳሰቢያ

3.1 በጉባዔው ላይ መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ስለሚወከሉበት ሁኔታ

በጉባዔው ላይ በአካል መገኘት የማይችሉ ባለአክሲዮኖች ተወካዮቻቸውን ሥልጣን ባለው የመንግሥት አካል ተረጋግጦ የተሰጠ የውክልና ሰነድ ዋናውን እና ፎቶ ኮፒውን በመያዝ ወይም በንግድ ሕጉ አንቀጽ 377 መሠረት ጉባዔው ከመካሄዱ ከሦስት ቀን በፊት በማህበሩ ዋና መሥሪያ ቤት (ዳኒ ፕላዛ፣ 4ኛ ፎቅ፣ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ፣ ወረዳ 02፣ አዲስ አበባ) በአካል በመቅረብ ለዚሁ ዓላማ በማህበሩ የተዘጋጀውን የውክልና ቅጽ ሞልተው በመፈረም ተወካይ መሾምና ተወካዩም የውክልና ማስረጃውን በመያዝ የጉባዔው ተሳፋይ ለመሆንና ድምጽ ለመስጠት የሚችሉ መሆኑን በአክብሮት እንገልጻለን። ሆኖም አንድ ባለአክሲዮን በማህበሩ ጠቅላላ ጉባዔ በማንኛውም ችሎታ መወከል የሚችለው አንድ ሰው ብቻ ስለመሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል።

3.2 ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው ስለሚያቀርቡት መታወቂያ

የአክሲዮን ማህበሩ ባለአክሲዮኖች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በጉባዔው ላይ ለመሳተፍ ሲመጡ ኢትዮጵያዊ ዜግነታቸውን ወይም ማንነታቸውን የሚያሳይ የታደሰ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ወይም መንጃ ፍቃድ እና እንደአስፈላጊነቱ የዲጂታል መታወቂያ ዋናውንና ኮፒ በመያዝ በጉባዔው ላይ መሳተፍ ይችላሉ። እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን የሆኑ የውጭ ሀገር ዜግነት ያላቸው የማህበሩ ባለአክሲዮኖች ትውልደ ኢትዮጵያዊነታቸውን የሚያረጋግጥ ቀዩን ያላለፈበት መታወቂያ (ቢጫ ካርድ) ይዘው መቅረብ እንዳለባቸው በአክብሮት እናሳስባለን።

ይህ የጥሪ ማስታወቂያ በማህበሩ ድረ-ገጽ የማስታወቂያ ሰሌዳ (https://pawapay.et/notice-board) ላይ ታትሟል።

የፓዋፔይ ዲጂታል ፋይናንሺያል አገልግሎቶች አክሲዮን ማህበር የዳይሬክተሮች ቦርድ

ቀን፦ ሰኔ **20** ቀን **2018** ዓ.ም **(June 27, 2026)** ቀን **2018** ዓ.ም